# <u>THE WALELEGN HIJACK STORY DECEMBER 1072</u>
## <u>AS TOLD BY ZERIHUN KEBEDE IN HIS BOOK ON HAILE SELASSIE (CHAPTER 64 AN EXTRACT IN AMHARIC)</u>

by Aleme Eshete

# <u>THE LAST HOURS OF WALELEGN</u>

***BY COURSEY OF DR. FIKRE TOLOSA***

***I saw Ato Walelign Mekonen for the last time 18 hours before he met his death in 1972. It was a night at the entrance of International Hotel in Arak Kilo, Addis Abba. He was coming out of the Hotel when my friend, Tesfay Yohanis and I were walking in. Tesfaye greeted Walelign and conveyed to him a message from Dr. Neugssie Ayele, Professor of Political Science at the then Haile Selassie I University. Walelign had been a political science student. Tesfaye told him that Dr. Negusse wants him to complete his thesis. Walelign snapped and said defiantly,*** *"ibakih zigga belew!"* ***(Tell him to shut up!). Walelign then worked at the Minstry of Ground Transportation together with Ato Gebru Mersha (now professor of political science at Addis Abeba University.)***
***Having said so, he drove off in a red, government Renault. Later, I gathered that he was driving around and coordinating the hijackers that night.***

***The following day, I heard over radio Ethiopia, that Walelign was dead together with six other people while attempting to highjack an Ethiopian airliner. Out of theseven hijackers two of whom were female, only Tadelech survived.  I knew three of them: Martha Mebratu, Getachew Habte and Tesfaye Birega. Martha was a medical student who had only one semester left before graduation. Tadelech was wounded, captured and imprisoned for years, until the Derg released her. I think she is now or was a Minister of Women's Affairs under EPRDF rule. Someone can correct me if she doesn't or didn't hold such a position.***

***The highjackers were reportedly led by an Eritrean, a member of the EPLF, who had been a student at the Haile Selassie I University before he joined the EPLF. He sneaked into Ethiopia bearing a Somali passport disguised as a Somali. This drew suspicion and the Emperor's security was alerted. They followed him around and observed the people he was meeting. He was meeting revolutionary students and former students. It didn't take long for the security to find out that the young people were scheming an airplane hijack. They decided to use the occasion to "liquidate" them. So, they let them board the airplane alerting their anti-hijackers that the revolutionaries were armed and dangerous. The rest is history. If the hijackers had succeeded, it was reported that they were heading for Algeria to join Berhane-meskel Redda and others who had hijacked another airplane about two years or so prior to that.***

***All had been in the blacklist of the government. Walelign, in particular, was under close surveillance. He had been jailed for months years before that for writing clandestinely a paper entitled, "Ye Awaju Awaj", which criticized the Emperor's speech (Awaj) against the student***

***movement. The Emperor's security failed to identify the writer of the article which ridiculed the Emperor. Amazingly enough, my friend, the poet-playwright Ato Mengistu Lema, told me then that it was the Emperor who identified the culprit. The Emperor read and reread the paper and got a clue that the writer was a Wolloye by a word he used in his writing,*** *(nedemot wey)*, ***or*** *"nedemeboty wey"* ***if I can correctly remember the word. I think it means*** *"Kochwot wey ቆጭዎት"* ***(do you regret it?) Ato Zewge Fanta or any other Welloye can tell us the meaning of*** *"nedeme"*, ***or if there is a word similar to that. The whole sentence read...***

*"Ye tahsas dem biyakajot( ቢያቃዣት ) yelekekutin betemengist silesetu**ስለሰጡ** nedemot wey?"*

***By that he was referring to the Neway brothers' execution of Emperor Haile Selassie's government officials inside the Green Salon of the palace during the December 1962(?) coup. I had read the paper myself at that time. I was a high school student in Dire-Dawa.***

***So much about my memoir of Ato Walelign Mekonen a night before he met his death. I am posting below an article I wrote in the Ethiopian Review magazine in July 1992 entitled "The Philosophy of Ethiopian Ethnicity", since it deals with Walelign and his thesis, and can also contribute something to the issue at hand and under discussion on this forum.***

***Fikre Tolossa***

---

## THE WALELEGN HIJACK STORY DECEMBER 1972<br>AS TOLD BY ZERIHUN KEBEDE IN HIS BOOK ON HAILE SELASSIE<br>(CHAPTER 64 AN EXTRACT IN AMHARIC)

# የዋለልኝ መኮንን የአይሮፕላን ጠለፋ ታሪክ /ኅዳር 29፤1965

**ከዘሪሁን ከበደ / የዓፄ ኃየለ ሥላሴ ታሪክ ፤ አዲስ አበባ 1993 ዓም፤**
**ምዕራፍ ስልሣ አራት**

## የከፍትኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾች

**ዋለልኝ መኮንን**
**ሄኖክ ክፍሌ**
**ታምራት ከበደ**

" እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸው የተገለጹት ሌሎቹን ጓደኞቻቸውን ጨምርው በኢትዮጵያና በውጭ አገር ያሉትን ተማሪዎች አነሳስተው የዓፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት እንጥላልን ብለው የተነሱ ነበሩ፣፣

ደግሞም በጣም የሚገርመው አባቶቻቸው በዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በታላቅ ስልጣን ላይ የነበሩ ከምሆናቸውም በላይ አማሮች ናቸው፤

ከመሀከላቸው ከድሀ ቤተ ሰብ የተገኘው ዋለልኝ መኮንን ብቻ ነው፤፤ ታምራት ከበደም ወላጅ አባቱ አቶ በላይ ሐድጉ መሆናቸው ቢታወቅም ፣ አስተምረው አቀማጥለው ያሳደጉት የዓጼ ኃይለ ሥላሴ የመከላከያ ሚንስትር የነበሩት ሌትና ጄኔራል ከበደ ገብሬ ናቸው፤፤ ፤፤

ሄኖክ ክፍሌ ማለት በዓፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለጠቅላይ ገዥነትና ለደጃዝማችነት ማዕረግ የበቁት የደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ ልጅ ነው፤፤

በአጭሩ እነዚህን እያቀማጠሉ አስተምርው ያሳደጉዋቸው ዓጼ ኃይለ ሥላሴ ናቸውለማለት ይቻላል፤፤ ተከሳሾች የዓፄ ኃይለ ሥላሴን መነግሥት ለመጣል የሚሠሩት ወንጀል ሁሉ ስለተደረሰባቸው በፖሊስ መርመራ ተጣርቶ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ ፣ ፍርድ ቤቱም የአቃቤ ሕጉን ምስክሮች ቃል አዳምጠ ይተጠራቀመውን ይጽሑፍ ማስረጃ አይቶ፣ የተከሳሾችን የመከላከያ ምስክር ሰምቶ ተከሳሾቹበተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ሆነው ስለተገኙ እየአንዳንዳቸው በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ፈረደባቸው፤፤

በፍርዱ መሠርት 5 ዓመት ቀርቶ ሶስት ወር ስይታሠሩ፣ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ ፣ አፈ ነጉሥ አበጀ ደባልቄ አማላጅ ሆነው ነጉሠ ነገሥቱን ለምነው አስፈቱአቸው፣

ዋለልኝ መኮንን በተፈታ ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ? ክጀብሐ ወንበዴዎች ጋር ተስማምቶ 7 እራሱን ሆኖ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መሥመር ቁጥር 720 ቦይንግ ጀት አይሮፕላን 94 መገድኞችን 9 ያይሮፕላኑን ሠራተኞች እንደያዘ በአሥመራ በኩል ወደ አቲንስ ሮምና ፓሪስ ለመብረር ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓም ከአዲስ አበባ የተነሳውን አይሮፕላን ሲጠልፍ በጀግኖቹ በቀልጣፎቹ ፀጥታ ጠባቂዎች ከአይሮፕላኑ ውስጥ ስድስት ራሱን ተገደለ፥

የዚህ አይሮፕላን ጠለፋን የውንበዴዎቹ አሟሟት እንዴት እንደነበር ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የተጻፈ ስለሆነ ቃሉን እንመልከት፣

@በአለፈው ዓርብ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይሮፕላንን ለመጥላፍ ሙከራ አድርገው የነበሩትን ወንጀለኞች ዓላማ ለማወቅ የፖሊስ ሠራዊት ሰሞኑን ስልፈጸመው ምርመራ ውጤት ትላንት ከዚህ ይሚከተለውን መግልጫ ሰጥቷል፣ ፣ ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓም የኢትዮጵያ አየር መገድ የበረራ መሥመር ቁጥር 730 ቦይንግ ጀት አይሮፕላን 94 መገድኞችና 9 የአይሮፕላኑ ሠራተኞች አሣፍሮ ከጥውቱ አንድ 1 ሰዓት ተኩል በአሥመራ በኩል ወደ አቴስ ሮም ፓሪስ ለመሄድ ከአዲስ አበባ ተነስቶ 13 ደቂቃ ያህል እንደ በረረ በወቅቱ ማንነታችው ያልታወቁ ወንበዴዎች ለማስገደድ በመሞከራቸው ክጥዋቱ 2 ሰዓት ከ55 ደቂቃ ተመልሶ አዲስ አበባ ቦሌ ኢንተርናሽናል አይሮፕላን ጣብያ አርፏል፣ ፣

"ሁኔታው እንደተሰማ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መነግሥት የፖሊስ ሠራዊት የደረሰው ምርመራ ቡድን በሥፍራው ላይ ተገኝቶ ባደረገው ምርመራ አምስት ወንዶችና ሁለት ሴቶች የጦር መሣሪያና ቦንብ ይዘው ለማስገደድ በመሞከር በአይሮፕላኑ ውስጥ ባስነሱት ተኩስ በተደረገው መከላከል ከአንዷ ሴት በቀር የተቀሩት በሙሉ ተገድለዋል፣ ፣

@ከዚህ በኋላ በተደረገው ጥብቅ ምርመራ አይሮፕላኑን አስገድደው ለመውሰድ የሞከሩት ፣

1. ዋለልኝ መኮንን
2. ማርታ መብራቱ
3. አማኑኤል ዮሐንስ (ማሳሳቻ ስሙን እየለዋወጠ በላይ ታደሰ መሐመድ ኡስማን መሐመድ የተባለ/
4. ጌታቸው ሀብቴ
5. ታደለች ኪዳነ ማርያም
6. ዮሐንስ ፈቃዱ
7. ተስፋየ ቢረጋ

የሚባሉት ናቸው፣

1ኛ.ዋለለኝ መኮንን ካሁን በፊት በፈጸመው ጥፋት በአምስት ዓመት እሥራት ተቀጥቶ ምሕረት ተደርጎለት በመንገድ ማመላሻና አስተዳደር መሥሪያ ቤት ይሠራ የነበረና የኤርትራ ነጻ አውጭ ድርጅት ነኝ ለሚሉት ወንበዴዎች ደጋፊ በመሆን ለተፈጸመው አደጋ ዋና መሪ፣

2ኛ. ወ/ት ማርታ መብራቱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲት የሕክምና ክፍሌጅ ተማሪ የነበረች፣ሌርትራ ነጻ አውጭ ወንበዴዎች በሐኪምነት ለመርዳት ፈቃዳ አውሮፕላኑን አስገድደው ክሚሄዱትጋር የተባበረች፣

3ኛ.አማኑኤል ዮሐንስ ኤርትራዊ ማሳሳቻ ስሙን እየለዋወጠ በላይ ታደሰ መሐመድ ኡስማን ወዘተ የተባለ፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበረ፣ ከወንበዴዎች ተልኮ በአይሮፕላን ጠለፋው የተባበረ፣ ሌሎቹን በማግባባትና ወደ ውንበዴዎች ለመውሰድ የሞከረ፣

4ኛ. ጌታቸው ሃብቴ የማዘጋጃ ቤት ጸሐፊ ለጅ የነበረ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ (ክፍሉ ታደሰ፣ ያ ትውልድ ክፍል አንድ ገጽ 70/ ፣ከኢትዮጵያ ከተባረሩት የውጭ ህገር ጋዜጠኞች ጋር ይሠራ የነበረ፣ አውሮፕላኑን በመሣሪያ ለማስገደድ የተባበረ፣

5.ተስፋዬ ቢረጋ በምድኃኔዓለም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ያስተምር የነበረ የወንጀሉ ተባባሪ

6ኛ.ወ/ት ታደለች ኪዳነ ማርያም በልዩ ለኡ ማስታወቂያ ድርጅቶች ትሠራ የነበር በዚሁ ሕግ ወጥ ተግባር ተባባሪ የሆነች

7ኛ. ዮሐንስ ፈቃዱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ 4ኛ ዓመት ተማሪ የነበረ፣ በወንጀሉ ተባባሪ፣

ሰባቱም ወንጀለኞች መሣሪያ ደግነውና ተኩሰው ለመጥለፍ መሞለራቸው በማስርጅ ተረጋግጧል፣ በልዩ ልዩ ዘዴ መሣሪያቸውን ይዘው ገብተዋል፣

ው/ት ማርታ መብራቱ ኮልት 38 ካሊበር የሆነውን ሽጉጥ ይዛ የገባችው በላስቲክ ጠቅላ በገመድ አስራ በጭኗ መሀከል ነው፣ በጠቅላላው ሁሉም በዚህ አኳኋን አውሮፕላን ላይ ተሳፍረው ል13 ደቂቃ በረራ ከተደርገ በኋላ አማኑኤል ዮሐንስ ቦንቡን ይዞ በመነሳት አውሮፕላኑን መጥለፋቸውን ሲአስታውቅ የቀሩት መሣርያቸውን በመንገደኞቹና በጸጥታ ሠራተኞች ላይ እየደገኑ እጃችሁን አንሱ በሚሉበት ጊዜ ዋለልኝ፡ መኮንንም መጀመሪያ ተኩስ በመክፈት አጠገቡ በነበረው ኢንስቴክተር ላይ ተኩሶ ጆሮ ገንዱን አቁስሎታል፣፣

ወዲያው ኢንስፔክተሮቹ በቀለጠፈ ሁኔታ ተከላክለው ይደመስሡ በነበረበት ጊዜ አማኑኤል ዮሐንስ ይዞት የነበረውን ቦንብ ወርውሮ በ8 መንገደኞችና በአውሮፕላኑ አስተናጋጆች እንዲሁም በሁለት ኢንስፔክተሮች ላይ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ሲደርስ በአይሮፕላኑ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ደርሶበታል፣

የወንበዴዎቹ ፍላጎትና ዓላማ ውጭ አግር ከሄዱ በኋላ መንገደኞቹንና አይሮፕላኑን መያዣ በማድረግ የኤርትራ ነጻ አውጭ ነኝ ለሚለው ድርጅት ገንዘብ ለመጠየቅ ነበር፣

ቀደም በሎ ሰባቱም ወንጀልኞች የተገደሉ መሆኑን መግልጫ መስጠቱ ይታወሳል፣ ነገር ግን ታደለች ኪዳነ ማርያም የተባለችው ከወንጀለኞቹ በተወረወረው ቦንብ ቆስላ ስለነበር ሕይውቷን ለማዳን በተወሰደው እርምጃ እስከአዛሬ በሕክምና ትገኛለች፣ የርሷ በሕይወት መኖር ያልተገለጸው በምርመራ ምክንያት ነው፣

ራሱን የኤርትራ ነጻ አውጭ ነኝ እየአለ የሚጠራው ድርጅት ቃል አቀባይ ትላንትና ከሊቢያ በሰጠው መግለጫ ባለፈው ዓርብ ዩትዮጵያ አየር መንገድ አይሮፕላን ለመጠላፍ የተደረገው ሙከራ የድርጅቱ ሃላፊነት ነው ሲል አስታውቋል፣

ቃል አቀባዩ ከዚህም በማያያዝ አይሮፕላኑን ለመጠለፍ የሞከሩት ይድርጅቱ ደጋፊዎች ዓላማ

አይሮፐላኑን ከያዙ በኋላ ለዚሁ ራሱን ዬርትራ ነጻ አውጭ አድርጎ ለሚጠራው ድርጅት ድጋፍ ለመስጠት ም እሆኑን አስታውቋል፣ ቃል አቀባዩ በአየሩ ውስጥ በተደርገው ውጊያ ሁለት የኢትዮጵያ የጸጥታ ጥበቃ አባሎች ተገድላዋል በማለት ከውነት የራቀ ወሬ አውርቶአል፣ የ94 መንገደኞችን ሕይውት አደጋ አፋፍ ላይ አድርሶ የነበረው የአይሮፐላን ጠለፍ ወንጀል በተፈጸመበት ጊዜ፣ በአየር ላይ ተኩስ የተጀመረው በጥላፊዎች መሆኑን ቢትዮጵያ አእውፋትን ለመመልከት የመጣው ቡድን አባል የሆኑት ሚስተር ሮድኒ ሲ ራይት ገልጠዋል፣ እንዲሁም ባይሮፐላኑ ላይ ከነበሩት ተሳታፊዎች መካከል አንድ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ በአየር ላይ ይተደረገው ተኩስ በመጀመሪያ የተጀመረው በጠላፊዎቹ ወንጀሎኞች መሆኑን አስረድተዋል፣

በኢትዮጵያ አዕዋፍን ለመመልከት ከእንግሊዝ አገር የመጣው ቡድን አባል የሆኑት ሮድኒ ሲ ራይት የተባሉት መንገደኛ ስለጠለፋው ሙከራ የሰጡት ሙሉ ቃል ከዚህ የሚከተከተለው ነው፣

@እኔ በቱሪስት ክፍል ውስጥ መጀመሪያ መቀመጫ ረድግተቀምጩ ነበር፣ አይሮፐላኑ ከመሬት ለቅቆ ሙሉ የጉዞ በረራ ላመጀመር እንደደርሰ አንድ ውጣት ከቱሪስት ክፍል በር ላይ በድንገት ብቅ ብሎሽጉጥ በመደገን ስል አይሮፐላኑ መጠለፍ ተናገር፣

በዚህም ወቅት ሠውየው ሽግጡን በፊት በተቀመጡት ሦስት ሰዎች ላይ ደግኖ በአንደኛው ሰው ላይ አንድ ጥይት ተኮሰ፣ ከተኩሱ በኋላ ሰውየው ከመቀመጫው መነሰቱን አስታውሳለሁ፣ ከዚህ በኋላ ብዙ ጥይቶች ተኮሱ፣ አንድ ቦንብ ፈነዳ፣ እንደምገምተው የመፈንዳቱ የተኩሱና የገርገሩ ሁኔታ የተፈጸመው ከሁለት እስከ ሶስት ደቂቃ ድራ ባላው ጊዜ ወስጥ ነው፣

በዚህ ጊዜ ውስጥ ሰባቱ አይሮፐላን ጠላፊዎች ስለተገደሉ ሁኔታው ጸጥ ብሎ ነበር፣ ሁላችንም በሕይወታችን ስናስታውሰው የምንኖረው በዚያን ወቅት የተካሄደውን ተኩስና ረብሻ ሰይሆን በፈነዳው ቦንብ የተጎዳውን አይሮፕላን ባስደናቂ ሁኔታ በመቆጣጠር ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ መልሶ ያሳረፈን አይሮፐላን ነጂ ዘዴና ጥበብ ነው፣ ከዚህም በላይ ሰባት የሚሆኑትን መሣሪያ የያዝ ጠላፊዎች በልዩ ፍጥነትና ቅልጥፍና ለማስወገድ የቻሉትን የፀጥታ ጠባቂዎችን ሥራ ሁላችንም በሕይወታችን ስናስታውሰው እንኖራለን፣
ከአደጋው በኋላ ከመጠን በላይ የሆነ የንክብካቤ ይዞታ ተደርጎልናል፣ የሆስፒታል ሠራተኞችም ከፍተኛ ትህትና ያሳዩን ሲሆን በዙ ሰዎችም ጎብኝተውናል፣

እንደምታውቁት ሁሉ ግርማዊንታቸውና ልዑል አልጋ ወራሽ እንዲሁም የንጉሠ ነገሥቱ ሚንስትሮች ጎብኝተውናል፣@

እንዲሁም አንድ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ በሰጡት ቃል፣
@እኔ በነበርኩበት ክፍል የመጀምሪያው ተኩስ የተጀመረው እኔ ላይ ነው፣ እኒም በዚሁ ጊዜ ቀኝ እጄን ተመታሁ፣ሽጉጡን ለይቾ ቁጥሩን ጠጋ ብዬ ለማየት አልቻልኩም እንጂ 38 ስፐሻል ይምስለኛል፣ ይጽጥታ ጥባቂዎችም ቅልጥፍና በዕውነቱ ከማስበውና ከምገምተው በላይ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፣ እንዲያውም አንዱ ጸጥታ ጠባቂ ከኔ አጠገብ ተቀምጦነበር፣ ከአይሮፐላን ጠላፊዎቹ አንዱ ወደኛ መጥቶ እጃችሁን አንሱ ባለን ጊዜ እጄን በማንሳት ፈንታ ስግደረደር ልመታ ቻልኩ፣ ይሁንና ጠላፊው እኔን በሽጉጥ ሲመታኝ ጸጥታ ጠባቂው በጁ መጥቶ ጣለው፣ተኩስ የተጀመረውም ከዚህ በኋላ ነው፣

በዚሁ ጊዜ አንድ ቀጠን ያለ ራሰ በራ ቦንቡን ይዞ እንደመጣ የጸጥታ ሠራተኛው ወደርሱ መሄድ ጀመረ ፣ በዚህ ጊዜ ጠላፊው ይህንን የያዝኩትን ቦንብ አፈነዳዋለሁ እያለና እየተሳደበ በማስፈራራት ላይ ሳለ ቦንቡን ጣለውና ተንከባሎ ወደኔ መጣና ልክ እኔ ዘንድ ሲደርስ ፈነዳ፣ ፍንጣሪው ዓይኔንና አልፎ አልፎም እግሪን አቆሰለኝ፣ በዚህ ዓይነት ሁከቱ በ 2 ደቂቃና 3 ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተፈጸመ፣ አይሮፐላኑ በአደጋው የተቀደደ በመሆኑ ይወድቃል ብለን ሰግተን ነበር፣ ነገርግን በካፒቴኑ ችሎታ ይሁን በእግዚአብሔር እርዳታ ተመልሰን አዲስ አበባ ገባን፣

ከዚህ በኋላ ወደ ሆስፒታል ተወስድን ከአሉ በኋላ በጸጥታ ጠባቂው ቅልጥፍና ቃል የማገኝለት አይመስለኝም፣በማለት አስረድተዋል፣፣ እኝሁ ሰው ተኩሱ እንዴት እንደተከፈተ ሲአስረዱ መጀመርያ የጥይት ተኩስ የከፈተው ዋለልኝ የሚባለው ነው፣ ከዚያ በኋል ከሁለት ጸጥታ ሠራተኛ ጋር ተያይዘው ወደቁ፣

ወዲያውም ቦንቡ ፈነዳ፣ ከዚህ በኋላ ሽጉጥ በብዛት ይተኮስ ጀመር፣ ቦንቡን አንድ የውጭ አገር ሰው አንስተው ሰው ወደሌለበት ክፍል ወረወሩት እየተባለ በውጭ አገር ጋዜጠኞች ስለሚነገረው ሲአስረዱ ከሰዎቹ ትንቅንቅ በኋላ ቦንቡ ስለወደቀ ተንከባሎ መጥቶ የፈነዳው እኔ አጠገብ ነው፣በዕውነቱ አንድ ጊዜ አንድ አሜሪካን ወረወርው አንድ ጊዜ አንድ ጀርመን ወረወረው  የሚባለው ፍጹም የተሳሳተ ወሬ ነው ብለዋል፣

በአይሮፕላኑ ላይ ከነበሩት መንገደኞች መካከል ዶክተር ዴሪክ ሂልስን ባሜሪካ የቴምፐል ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር በተናገሩትም ቃል በቱሪስት ክፍል በሁለተኛው መስመር ላይ ተቀምጬ ሳለሁ አንድ ሰው ተነስቶ ወደፊት ከሔደ በኋላ ወዲያውኑ ፊቱን ዘወር አድርጎ አይሮፕላኑ መጠለፉን ተናገረ፣ ከዚያም ከፊቴ ተቀምጦ የነበረው አንድ የጸጥታ ሠራተኛ ከመቀመጫው ዘለልና ተናጋሪውን ሰው ከመቅጽበት በእጁ ሲመታና ከወልወሉ ላይ ሲዘርረው አየሁ፣ በዚህ ጊዜ ሌላ ሰወ የጅ ቦንብ ይዞ በትከሻዬ በኩል ቆሞ ነበር፣ ቦንቡ ወልወል ላይ ወድቆ እንዳየሁ ከመፈንዳቱ በፊት የማፍንበትነ ትራስውይንም ምናኝውንም ነገር ከተቀመጥኩበት ሥፍር በላይ ካለው የቃ ማስቀመጫ ላይ ለመፈለግ ብድግ እንዳልኩ ከመመልሴ በፊት ፈንዳ፣ አኒም ትከሻዬ ላይ ከራሴ ላይና ከግሬ ቁርጭምጭምቴ ላይ በመመታቴ ሕሊናዬን ስቼ ስለነበር የዓይን ምስክርነቴ ይህ ብቻ ነው፣

ከዚህ ሌላ ከሳንፍራንሲስኮ ካሊፎርኒያ የመጡት ጆን ኦ ኮኖር በበኩላቸው በሰጡት ቃል ተኩሱና ረብሻው በተነሣ ጊዜ ከፊት ለፊት በሚገኘው ክፍል ውስጥ ተኝቼ ነበር፣ አብዛኛው የጥይት ተኩስና ረብሻ የተካሄደው በቁጠባ የመጓጓዣ ክፍል ውስጥ ነበር፣ በአንደኛ ማእርግ መቀመጫ ላይ ስለነበርኩአብዛኙውን ጊዜ ቦንቡ እስከፈንዳበት ጊዚ ድረስ በብዛት አልተመለከትኩም፣ አንዱ ጓድኞችን በመቁሰሉ እሱን በመርዳት ላይ እንዳለሁ ክፍሉ በሙሉ በጭስ ተሸፈነ፣ እንዲሁም ከተሰበረው የውሃ ማጠራቀምያ ታንክ የመጣው ውሃ ክፍሉን  ሞላው፣@

ይህ ከዚህ በላይ ያቀረብነው ሪፖርት ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያገኘነውን ነው፣

አንባብያን በጽሑፉ እንደተረዳችሁት በአይር ላይ የተደረገው ጦርነት  7 ለ 2 ነው፣ ለበ ሙሉ ጀግኖች የሆኑት የጸጥታው ጠባቂዎች  ከመቁሰል በቀር አንዳቸውም ሳይሞቱ ሁለት ሁነው ሰባቱን ወንበዴዎች  በአየር ላይ ጦርነት ገጥመው ድል ስለአደረጉ ሰባቱንም ወንበዴዎች አረፍርፈው ግድጃቸውን ስለተወጡ እጅግ በጣም ሊመሰገኑ የሚገባቸው ጀግኖች ናቸው፣

በቦንቡ ፍንዳታ ምክንያት በአይሮፕላኑ ላይ ከፍተኛ የሆነ ብልሽት ደርሶበት እንደነብር ምስክሮቹ በሰጡት ቃል ለመረዳት ችለናል፣ ነገር ግን አይሮፕላኑን ይነዳ የነበረው ጀግና ካፕቴን ቀጸላ ሃይሌ ሳይሸበርና ሳይርበደበድ በልበሙሉነት በታላቅ ጥበብና ጥንቃቄ ከአደጋው በኋላ ፊቱን ወደ አዲስ አበባ አዙሮ ክ 10 ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ተጉዞ አይሮፕላኑን በደህና አሳርፎ በአይሮፕላኑ ውስጥ የነበሩትን 94 መንገደኞች 9 ያይሮፕላን ሠራተኞች ሕይወት በማትረፉ ሊመሰገን የሚገባው ጀግና ፓይለት ነው፣

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ይህን የመሰለውን አደግ ለመጠበቅ በአይሮፕላኑ ይሠማሩ የነበሩት ፀጥታ ጠባቂዎችች የዚህ ዓይነቱ ፈተና ሲአጋጥማቸው ግዳጃቸውን በድል ለመወጣት ልምድ በበራቸው፣ ከዚህ አደጋ በፊት ታህሣሥ 3 ቀን አ962 ዓም ንብረትነቱ ዬትዮጵያ የሆነ ቦይንግ 707 የአይሮፕላኑን ሠራተኞሽ ሳይጨምር 25 መንገደኞች አሳፍሮ ከማድሪድ ወደ አቴንስ ሲበር በሁለት የአረብ ወንበዴዎች ስልተጠልፈ አሁን እንደተደረገው ፈጣኖቹን ጀግኖቹ ለጀቻችን  ወዲያውኑ ከመቅጽበት  ሁለቱንም ጠላፊዊች በአይር ላይ ገድለዋቸዋል፣ እንዲህም በተደረገበት ጊዜ በተሳፋሪዎቹም ሆነ በይሮፕላኑ ላይ አንድም የደርሰ ጉዳት አልነበረም፣

ወዲያውም መርመራው ሲጣራ ወንበዲዎቹ የሶርያ አረቦች ሆነው ተገኝተዋል፣... አረቦች ኢትርትራን ከኢትዮጵያላማስገንጠል  ፊትም ለጅብሃ በኋላም ለ ያድርጉት የነበር ዕርዳታ  በገንዘብና በጦር መሣሪያ ብቻ ስይወሰን የሕይወት እርዳታም ያደርጉ እንደነበር የነዚህ ሁለት አረቦች ሬሳ ምስክር ነው፣ እንዚህ አረቦች በተገደሉበት ወቅት  ቤርትራ የወንበዴዎች ዋና ሆኖ ይን ቀሳቀስ የነበረው ጀብሃ ነው፣

አረቦች ኤርትራን ከኢትዮጵያ አስገንጥለው ቢቻል ከአረቦች የአንዳቸው ግዛት እንድትሆን፣ይህም እማይቻል ቢሆን የእስላም መንግሥት አቋቁመው የአረብ ሊግ ጭፍራ እንድትሆን ነበር፣ ነገር ግን በተገነጠልች በንጋው ከአረብ ጠላት ከኢትዮጵይ ወዳጅ ከሆነችው ከእሥራኤል ጉያ ሄዳ ስልተለጠፈች ያረቦችን አንጀት በእሳት እንደተቃጠለ ጅማት ሲአሳርረው ኢትዮጵያውያን ግን በደስታ ብዛት አንጀታችን ተርክሷል፣

//////////////////////////////

አሁን ወደ ተነሳሁበት ታሪክ ልመለስ፣ ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓም በአይሮፕላኑ ውስጥ ከነበሩት 7 ወንበዴዎች ስድስቱ እዚያው አይሮፕላኑ ውስጥ 3 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሲደመሰሱ፣ አንዷ ወንበዴ ታደለች ኪዳነ ማርያም ከግብር አበሯ አማኑኤል ዮሐንስ በተወረወረው ቦንብ ስልቀሰለች የጸጥታ ሠራተኞች እንደ ጓደኞቿ ከዚያው ሊጨርሷት ሲችሉ አንድ ቁስለኛ ከተማረከ በኋላ መግደልን ሕግ እንድማይወደው አውቀው አልገደሏትም፣

አይሮፕለኑ ከወረደ በኋላም መንግሥት ምንም ዓይነት አድሎ ሳያደርግባት እንደሌሎቹ ታካሚዎች በአስቸኳይ ፖሊስ ሆስፒታል እንድትገባ አድርጎ ደርግ እስኪመጣ ስትታከም ቆይታለች፣

የሞቱትን የስደስት ወንበዴዎች አስከሬን መንግሥት ከአይሮፕላን በክብር አውርዶ ለቤተሰቦቻቸው አንዲሰጥ አድርጓል፣ የዋለልኝ መኮንን ቤተሰቦችም አስከሬኑን ተረክበው ባይሮፕላን አሳፍረው ወደ ትውልድ አገሩ አእደ ወሎ ይዘውት ሄደዋል፣ ደሴ ከተማ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስትያን ወዳጅ ዘመድ በአለበት በክብር ተቀብሮአል፣ በቀብሩ ጊዚም የጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ድጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም፣ ም/ እንደራሴው ደጃች ከበደ አሊ ወሌ የየምኒስትሩ ተወካዮች ተገኝተዋል፣ እኔም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ሁኘ እዚያው እሥራ ስለነበር በቀብሩ ተገኝቻለሁ፣

እዚህ ላይ አንባቢዎች ልብ አድርጋችሁ ልትመለከቱት ይሚገባ አንድ ነገር አለ፤፤ የንጉሠ ነገሥሩ እንደራሴና ይየምኒስትሩ ተወካዮች እኔም ራሴ የቀብሩ ሥነ ሥራዓት መገኘታችነ ነው፤፤ የዚህ ዓይነቱን ወንጀል በደርግ ወይም በወያኔ ጊዜ ሲፍጽም ተገኝቶ የተገደለ ሰው ከሁሉ አስከሬኑ ለማንም አይሰጥም፤፤ ቢሰጥም እንኳ ጠቅላይ ገዥውና የየሚኒስትሩ ተወካዮች ይቅርና ማንም ተራ ሰው ወጥቶ እንዲቀብር አይፈቀድለትም፤፤

በ1986 ዓም በመጋቢት ወር አይሮፕላን ሲጠልፉ ተገኝተው ድሬዳዋ ላይ በመንግሥት ጸጥታ አስከባሪዎች ሁለት ጠላፊዎች መገደላቸውን መላው ዪትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ፣ የነዚህ ሰዎች አስከሬን ለቤተሰቦቻቸው መሰጠቱ ይቅርና የት እንድተጣሉም አይታወቅም፤፤

ስልዚህ በዓጼ ኃይል ሥላሴ ዘመነ መንግሥትና በደርግ በወያኔ ጊዜ ያለውን የነፃነት ልዩነት ምን ያህል የተራራቀ መሆኑን በዚህ ልትረዱት ትችላላችሁ፤፤

ድጃዝማች ታከለ ወለደ ሐዋርያት ዓጼ ኃይለ ሥላሴን ለመግደል ብዙ ጥረት ሲአድርጉ ተገኝተው፣እጃቸውን ለፖሊስ እንዲስጡ ሲጠየቁ አልስጥ በልው የገዛ ሽጉጣቸውን ጠጥተው በሞቱ ጊዜ ከአልጋ ወራሹ ጀምሮ ወደ ታች የአሉት ባለስልጣኖች በቀብራቸው ተገኝተዋል፤፤ ይህን ባመድረጋቸውም ምንም የደረሰባቸው ነገር የለም፤፤

ኤርትራን ለመገንጠል ጥረት ከሚአደርጉት ወንበዴዎች ጋር ተባብሮ ወልዳ አሳድጋ አስተምራ ለቁም ነገር ያበቃችውን አገሩን ኢትዮጵያን ከድቶዪትዮጵያ ሃብትና ንብረት የሆነውን አይሮፕላን ሲጠለፍ ተገኝቶ የተገደለውን ወንበዴ ሄጄ በመቅበሬ ዛሬ ሳስበው ይቆጨኛል፣ የነጻነት ብዛት ልብ ያሳጣል ልበል?

ወያኔ ከደርግ (የኢትዮጵያ/ ሠራዊት ጋር እየተዋጋ ወደ መሀል አገር በሚገሰግስበት ጊዜ በጎንደር ለከፈተው ጦርነት የቴዎድሮስ ዘመቻ በውሎ ለከፈተው ጦርነት የዋለልኝ ዘመቻ ብሎ መሰየሙን ሁላችንም የምናውቀው ነው፣ በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ ለ72 ዘመን ያህል የቆየችውን አገር 18 ጊዜ ተውግተውና

ድል አድርገው ኢትዮጵያን አንድ  ከአደረጉት ከቴዎድሮስ ጋር ዋለልኝን  እኩል አድርጎ መሰየምና...ኤርትራን እንገነጥላልን ብሎ ለተነሳው ወንበዴ አሽከር ሁኖ አገሩን ኢትዮጵያን ሲበድል ተገኝቶ በመገደሉ እንደ ትልቅ አርበኝነት ( መቁጠር ምን ይባላል፣/

ዋለልኝ ...የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት የሆነውን አይሮፐላን ጠልፎ ከኢትዮጵያ እገነጠላለሁ ብሎ ለተነሳው ለጀብሓ ገዳይ ለመጣል መሞከር የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ሊጥለው አይችልም፣ ጉብዝና ካለው ሰላማዊ ሕዝብ የተሳፈረበትን አይሮፐላን ጠልፎ በሰማይ ላይ ተኩስ ከመክፈት ጫካ ገብቶ ትግሉን መቀጠል ነበረበት፣

ዋለልኝ መኮንን ከፊደል እስከ ዩኒቨርሲቲ አስተምራ ይስድቀመጥቸው  ጥፋት ሠርቶ አምስት ዓመት እሥራት ተፈርዶበት  3 ወር ስይታሰር ምህረት አድርጋ የፈታችው ኢትዮጵያ እንጂ  ኤርትራ ውይም ጀብሐ አይደለችም፣ ማርት መብራቱንም ወልዳ አሳድግ ከፊድል እስከ ዩኒብርሲቲ ያስተማረች ኢትዮጵያ እንጅ ጀብሐ ውይም ኤርትራ አይደለችም፣ እንኳን እሷን አባቷንም ከልጅነት እስክ ዕውቀት ያሳደገች ለብ/ ጀኔራልነት ማዕረግ ያበቃች ኢትዮጵያ እንጂ ጀብሐ ወይም ኤርትራ አይደለችም፣፣ ታደለች ኪዳነ ማርያም ያደገችው አድዋ ነው፣...

ከ1962 ዓም ጀምሮ ኢሕአፓ ተብሎ ይሚጠራ ድርጅት ተመሥርቶ የዓፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመጣል የሰላ መጋዙን ይዞ ይገዘግዝ ጀመር፣ በዚህ ድርጅትም በይበልጥ የተሰገሰገው  ያ ደንቆሮ ቂሉ የአማራው ተወላጅ ነኝ የሚለው ነበር፣ የገዛ መንግሥቱን ለመጣል ያንን ሁሉ ታግሎ እንደጧፍ ተቃጥሎ ከአጼ ይኩኖ አምላክ  ክ1262 ጀምሮ 700 ዓመት ፀንቶ እንድ ብረት ጠንክሮ የኖረውን የገዛ መንግሥቱን በአፍ ጢማራው ደፍቶ ኢትዮጵያ ልትወጣው ወደማትችለው የመከራ አዘቅት እንድትገባ፣ ኤርትራ እንድትገነጠል፣ አንድ ትውልድ ሕዝብ እንዲያልቅ የኢትዮጵይ ሀብትና ነብረት እንዲወረስ፣ ሕዙቡ ከድህነት እንዲወድቅ፣ ፊትም ለደርግ በኋላም ለወያኔ መግሥቱን አስረክቦ እሱ የጥይት እራት ሁኖ ጉድጓድ ገብቶ፣ አፈሩን  ተሸክሞ ቀረ፣፣

እንደውም ሀገሪቱ ይህን ለመሰል መከራ ከመዳረጓም በላይ በብዙ ድካም በብዙ ሙግት ያስመለሷትን ኤርትራን አንድትገነጠል አደረጓት፣

የአፄ ኃይለ ሥላሴ መገደል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብልጽግና ማስገኘቱ ቀርቶ እንዲያውም በርሳቸው ጊዜ ያፈራውን ሀብትና ንብረት ተቀምቶ ሊውጣው ከማይችለው አዘቅት ወድቆ ይገኛል፣፣

//////////////////////////////////////////////////

(ከዚህ በላይ የቀረበውን ሪፖርት ትክክለኛነት ልታረጋግጥልን የምትችለው ዛሬ ሕይወቷ ተርፎ በሆላንድ የምትገኘው ታደለች ኪዳነ ማርያም ብቻ ስትሆን እርስዋንም የቀድሞ ባለቤቷ ወዳጇ ዘሩ ከህሽን በሕይወት እያለም ሆነ ከዚያ በኋላ አግኝቼ ስለዚሁ ታሪክ ላነጋግራት እስካሁን ዕድሉ አልገጠመኝም፣ አሁንም መሞከሪን አላቆምም፥፥/